# የግሎባል ቪዥን ሪፖርት በምጥኑ

## አሥሩ ዋና ዋና ቁልፍ ጉዳዮችና መልካም አጋጣሚዎች



**190**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሀገራት በ7 አህጉራት

**469,152**

ዓመታት የቤተመጻሕፍት አገልግሎት

**ለሁሉም**

ትውልዶችና የቤተመጻሕፍት ዓይነቶች

**9,291**

የወርክሾፕ ተሳታፊዎች

**185**

ወርክሾፖች

**21,772**

የኦንላይን የምርጫ ድምጾች

IFLA Global Vision

# ቁልፍ ግኝቶች

**በግቦቻችን እና በመርሆዎቻችን ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአንድነት ቆመናል**
አንዱ እጅግ ጠቃሚ ግኝት በየትኛውም ክልል፣ የቤተ-መጸሕፍት ዓይነት እና የቤተመጸሕፍት አገልግሎት ልምድ መጠን ሳንገደብ በቤተ=መጸሕፍቶች በዘመን የማይወሰን ጠቃሚ ሚና እና ግብ ባለን ቁርጠኝነት ላይ በጋራ ቆመናል።

**ዓለም አቀፍ እና አካባቢያዊ ተግባራቶቻችንን በውጤታማነት ማቀና  ት ይኖርብናል**
የቤተመጻሕፍት ሴክተር ለጋራ ፈተናዎች መፍትሔ ለመስጠት እንዲችል ለማስተባበር ለምናደርገው የወደፊት ጥረት የአካባቢዎችን ልዩ ጸባያትና ፍላጎቶች ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

## 10 ዋና ዋና ጉዳዮች

### 1. መረጃ እና እውቀትን በእኩልነትና በነጻነት ማግኘት እንዲቻል በጽናት እንሰራለን

በማናቸውም የቤተ-መጻሕፍት ሴክተር ውስጥመረጃና እውቀትን በነጻነትና በእኩልነት በማግኘትረገድ ያለንን ጽናት የሚወዳደር ሌላ መርህ አይገኝም።

### 2. ከመሃይምነት መላቀቅን፣ መማር እና ማንበብን ለመደገፍ ያለን ጽናት በዘላቂነት ይቀጥላል

ከረጅም ጊዜ  ምሮ አብረውን ያሉት ጥንካሬዎቻችን ማለትም መማርን፣ ከመሃይምነት መላቀቅን እና ማንበብን መደገፍ ለቤተ-መጻሕፍት ሥራ ተልዕኮዎች ዋና መሠረት የመሆናቸው ጉዳይ ዓለም-አቀፍ እውቅና አግኝቷል።

### 3. ማህበረሰባችንን ለማገልገል ዝግጁ ነን

ማህበረሰብን በምንም መልኩ እንግለጸው እንጂ የተጠቃሚዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ባለን ተልዕኮ ላይ የጋራ አቋም አለን። ለብዝሃነት፣ ለአሳታፊነትና ከንግድ ነጻ ለሆነ ህዝባዊ አገልግሎት አቅርቦት ከፍ ያለ ዋጋ እንሰጣለን።

### 4. የዲጂታል ፈጠራዎችን እናበረታታለን

የቤተ-መጻሕፍት ሙያ የዲጂታል ፈጠራዎች (የሚጠቀሙት ቴክኖሎጂ መጠን ምንም ያህል ቢሆን እንኳን) ቤተ-መጻሕፍት የማህበረሰቡን አቅም ለማዳበር እንዲችል በመርዳት ረገድ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ መሆኑን በእጅጉ ይቀበላል።

## 10 መልካም አጋጣሚዎች

### 1. የምሁራዊ ነጻነት መብት ጽኑ ደጋፊዎች ልንሆን ይገባል

መረጃና ዕውቀትን በእኩልነትና በነጻነት የማግኘት ጉዳይ ሃሳብን በመግለጽ ነጻነት ላይ ይመሰረታል። ይህን በማረጋገጥ ረገድ የቤተ-መጻሕፍት ሚና ምን እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

### 2. ተለምዷዊ ሚናችንን ወደ ዲጂታል ዘመን ማሳደግ ይኖርብናል

በዚህ የዲጂታል ዘመን መማርን፣ ከመሃይምነት መላቀቅን እና ማንበብን ትርጉም ባለው ሁኔታ ለመደገፍ ቤተመጻሕፍት በማያቋርጥ ሁኔታ ራሳቸውን ከጊዜው ጋር ማራመድ ይገባቸዋል። አገልግሎቶች ስብስቦችና ድርጊቶች በየጊዜው የሚለዋወጠውን የተጠቃሚዎች ፍላጎት ለማሟላት በሚያስችል ሁኔታ ማደግ ይኖርባቸዋል።

### 3. የማህበረሰቡን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ መረዳትና አገልግሎቶችም ውጤታማ እንዲሆኑ ተደርገው መቀረጽ ይኖርባቸዋል

ስለቤተ-መጻሕፍት ጠቃሚነት የሚደረጉ ሕብረተሰባዊ ገለጻዎችን ማስፋፋት በአካባቢው ከሚገኙ አጋሮች ጋር ጥምረት ለመፍጠር፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ አዲስ እና አገልግሎት ያላገኙ ክፍሎችን ለማሳተፍ እና በሰዎች ሕይወት ላይ ያሳረፈውን ተጽዕኖ በሚለካ ሁኔታ ለመመዘን ይረዳል።

### 4. በየጊዜው እያደገ ከሚሄደው የቴክኖሎጂ ለውጥ ጋር እኩል መራመድ ይኖርብናል

ሁሉም ቤተ-መጻሕፍት የዲጂታል ፈጠራዎች በሚፈጥሯቸው ዕድሎች ለመጠቀም ተገቢው መሣሪያዎች፣ መሠረተ ልማት፤ ገንዘብ እና የሰው ሃይል ያላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

### 5. ጠንካራ የማስተዋወቅና የማስረጽ ሥራን አስፈላጊነት የሚረዱ መሪዎች አሉን

በእኛ አመራር ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ከመሪዎች፣ ከተጽዕኖ ፈጣሪዎች እና ከሰፊው ማህበረሰብ ጋር ስለቤተ-መጸሐፍት አስፈላጊነት የማያቋርጥ የማስተዋወቅና የማስረጽ ሥራ መሰራት እንዳለበት ይገልጻሉ።

### 6. የፋይናንስ አቅም እጥረት ካሉብን ችግሮች ውስጥ ዋነኛው እንደሆነ እንረዳለን

የገንዘብም ሆነ ቁሳዊ  ብቶችን ለማግኘት መቻልና እነዚህኑ ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ለህብረተሰቡ ፍላጎት በተገቢው መልኩ ምላሽ የመስጠት አንዱ አስፈላጊ አካል ነው።

### 7. ትብብር እና አጋርነትን መገንባት ጠቃሚ መሆኑን እንገነዘባለን

ጠንካራና የተባበረ የቤተ-መጸሐፍት ሙያን ለመፍጠር በእኛ መካከል ትብብር እና ከእኛውጭ ካሉ አካላት ጋር አጋርነትን በመፍጠር መሥራት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እንገነዘባለን።

### 8. ቢሮክራሲያዊነትን፣ ግትርነትን እና ለውጥን አለመቀበልን መቀነስ ይኖርብናል

የቤተ-መጸሐፍት ሙያ በአቀራረቡ የቀዳሚነት፣ ለፈጠራ ክፍት የመሆንና ኋላ ቀርና ጎታች ተግባራትን የማስወገድ ፍላጎትን ይጋራል።

### 9. የዓለም የእሳቤ መረጃዎች ጠባቂዎች ነን

ቤተ-መጻሕፍት የዓለም የሰነድ ቅርሶችና በውስጣቸው የያዟቸው ሃሳቦችና ፈጠራዎች ቀዳሚ ጠባቂዎች ናቸው። እኛ በተለየ ሁኔታ ለመጭው ትውልድ እውቀትን ጠብቆ በማቆየት እና አደራጅቶ በመያዝ ረገድ ችሎታ አለን።

### 10. ወጣት ባለሙያዎቻችን ውጤታማ ለመሆን ትጋት ያላቸው እና መሪ ለመሆንም ጉጉዎች ናቸው

ለሙያው ገና አዲስ የሆኑ ሰዎች በሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን የሚያሳዩት መነሳሳት የቤተ-መጻሕፍት ሙያን የወደፊት ዕጣ ለመወሰን በሚደረገው ጥረት ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸውን ጉጉት ያመለክታል።

### 5. በሁሉም ደረጃዎች በብዛትም ሆነ በተሻለ ሁኔታ የማስተዋወቅና የማስረጽ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ያስፈልጉናል

በሙያው ውስጥ ያሉ ሰዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችን ለማሻሻልና በመጨረሻም ከግቦቻችን ለመድረስ የማስተዋወቅና የማስረጽ ሥራ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በጥልቅ ሊገነዘቡ ይገባል።

### 6. ባለድርሻ አካላት ዕሴቶቻችንን እና የምናሳድረውን በጎ ተጽዕኖ የተረዱ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል

ቤተ-መጻሕፍት መልካም ዕሴት ለመፍጠር የሚችሉ መሆኑን አበክሮ ማስገንዘብ ዕውቅናን ለማግኘት የሚረዳና ከውሳኔ ሰጭዎችም ድጋፍ ለማግኘት የሚረዳ ነው።

### 7. የትብብር መንፈስ እንዲሰፍን መጣር ይኖርብናል

ለትብብር እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ማወቅና መፍትሄ መስጠት ተነጥሎ ለብቻ የመስራት አዝማሚያን የሚከላከልና የተባበረ የቤተመጻሕፍት ሙያ ራዕይ እውን እንዲሆን የሚረዳ ነው።

### 8. 8. በሥራ ላይ ያሉ መዋቅሮችንና አስተሳሰቦችን መፈተን ይገባናል

ተነሳሽነት ከሚጎድለው አስተሳሰብ ለመውጣት መቻልና ፈጠራ እና ለውጥን መቀበል የቤተ-መጻሕፍት ሙያ የሚገጥሙትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለማለፍ ይረዳናል።

### 9. በዓለም የሰነድ ቅርሶች ለመጠቀም መቻልን ማበረታታት አለብን

እንደ አንድ የተባበረ ሙያ የፈጠራ ችሎታ ያለባቸውን ተግባራትና መጠቀሚያ መሣሪያዎችን ተግባር ላይ ማዋል፣  ብትና ልምድንመካፈል፣ የሕግና የገንዘብ ማነቆዎች መፍትሔ እንዲያገኙ መታገል እና በእጃችን በሚገኙ ሥራዎች ሰዎች እንዲጠቀሙባቸው ማድረግ ይገባናል።

### 10. ወጣት ባለሙያዎች ለመማር፣ለማደግ እና ለመምራት የሚያስችላቸውን መልካም ዕድል ልናቀርብላቸው ይገባል

ወጣት የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያዎች እንዲያድጉ እና ግንኙነት ለማድረግ እንዲችሉ ሙያው ያለው ብቃት ከተለዋዋጭ ፍላጎቶች ጋር እኩል ለመራመድ መቻል ያለበት ሲሆን ወጣቶቹ የመጭው ዘመን መሪዎች ለመሆን እንዲችሉ መደገፍ ይኖርበታል።

# ራዕያችን፣ የመጭው ዘመን ተስፋችን፡


## ጠንካራ እና የተባበረ የቤተ-መጻሕፍት ሙያ ከመሃይምነት ነጻ ለሆነ፣ በቂ መረጃ ላለውና ተሳታፊ ለሆነ ሕብረተሰብ በቂ አቅም ለመስጠት

ከምንጊዜውም በላይ እየጨመረ በመጣው ግሎባላይዜሽን ምክንያት የቤተ-መጻሕፍት ሙያ እየገጠመው ያለውን ፈተና መቋቋም የሚቻለው አሳታፊ እና ዓለም-አቀፍ በሆነ የተባበረ የቤተ-መጻሕፍት ሙያ ምላሽ ብቻ ነው። ለዚህም ነው ዓለም-አቀፍ የቤተ-መጻሕፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን የመጭውን ዘመን የተባበረ የቤተ-መጻሕፍት ሙያ ፍኖተ-ካርታ ለማበ  ት የሚረዳውን የግሎባል ቪዥን ውይይት የ  መረው።

እያንዳንዱ በመላው ዓለም ላይ የሚገኝ የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያ የሚሳተፍበት ይህን መሰል ጅማሮ ከዚህ በፊት ያልታየ ሲሆን ከበርካታ የዓለም ክፍሎች ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያዎች ለዚህ ዓለም-አቀፍ ውይይት አስተዋጽዖ ሲያደርጉም በተመሣሣይ ሁኔታ መቼም ቢሆን ታይቶ የማይታወቅ ነው።

በ2009 ዓ.ም. ዓለም-አቀፍ የቤተ-መጻሕፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን በመላው ዓለም የሚገኙ ቤተ-መፃሕፍት እየገጠሟቸው የሚገኙ ችግሮችና እንዲሁም ያሏቸው መልካም ዕድሎች ምን እንደሆኑ ማጥናት   መረ፡ ፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ከሆኑ በሰባቱም ክፍለ አህጉሮች ከሚገኙ 190 አገሮች የደረሰው ምላሽ በግቦቻችን እና በእሴቶቻችን ላይ ምን ያህል የተባበርን እንደሆነ ያሳየ ነው። ይሁንና ዓለም-አቀፍ እና አካባቢያዊ ድርጊቶችን በውጤታማነት ማጣመር ይኖርብናል። የእያንዳንዳቸውን ክልሎች ልዩ ሁኔታዎችና ፍላጎቶችን በቅጡ መገንዘብ የቤተ-መፃሕፍት ሙያ ለጋራ ችግሮቻችን መፍትሔ ለመስጠት እንዲችል ለማስተባበር ለምናደርገው የወደፊት ጥረት እጅግ አስፈላጊ ነው።

አሁን ደግሞ በዚህ የ2010 ዓ.ም. ዓለም-አቀፍ የቤተ-መጻሕፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ለመላው የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያዎች አነቃቂ የሆነ እና ፌዴሬሽኑ ለመጭው ዘመን ለሚነድፈው ዕቅድ ለተግባራዊነት የሚረዳ ትልቅ የሃሳብ ቋት እያዘጋ  ይገኛል። በተለያዩ ዎርክሾፖች እና የኦንላይን መድረኮች አማካይነት በመላው ዓለም ከሚገኙ የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያዎች ሃሳቦችን ለማሰባሰብ እንፈልጋለን። ይህም ሁሉም ክልሎችና የቤተ-መጻሕፍት ዓይነቶች ምን ሚና መጫወት እንደሚችሉ ለማወቅ ይረዳናል። እርስዎ በሚያቀርቡት ሃሳብ ዓለም-አቀፍ የቤተ-መጻሕፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ራዕዮቻችንን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና የተግባር ዕቅዶችን ለመንደፍ ይችላል - ጠንካራ እና የተባበረ የቤተ-መጻሕፍት ሙያ ከመሃይምነት ነጻ ለሆነ፣ በቂ መረጃ ላለውና ተሳታፊ ለሆነ ሕብረተሰብ በቂ አቅም ለመስጠት!




#iflaGlobalVision

ifla.org/globalvision